# እድሜ

እድሜ ከጤና ጋር እግዜር የወደደው፤
እድሜ ከገንዘብ ጋር ዓለም የሚያደንቀው፤
እድሜ ከመጠጥ ጋር ሞት የናፈቀው፤
እድሜ ከችግር ጋር ሰው የሰለቸው፤
እድሜ ከሰላም ጋር ሁሉ የሚመኘው::

እድሜ የበዛለልህ እጅግ ደስ ይበልህ፤
ኩራት ይገባሀል እድሜ ላስተማረህ፤
ገንዘብ ባይኖርህም እውቀትህ ነው የግልህ፤
የዓለምን ተፈጠሮ በጥረህ እንድታይ ጊዜ የሚሰጥህ::
እያንዳንዷን አመተህን ተጠቀምባት አክብረህ አድንቀህ፤
እንዳንተ ዕድሜ የታደለው ብዙ እንዳልሆነ አውቀህ፤
አትሸማቀቅ አትፍራ እድሜህን ሲጠይቁህ፤
ተመስገንን ልመድ እድሜ ስጦታ መሆኑን አውቀህ::

ከ ኒኒ ለገሰ